# አሜሪካኖችና የሰብአዊ መብቶች መከበር ጥያቄ በኢትዮጵያ

አክሎግ ቢራራ (ዶር)

ኢትዮጵያን በሚመለከት በዚህ ወር በአሜሪካ ምክር ቤት ሁለት ያልታሰቡ ውይይቶች ተካሂደዋል፤ አንድ የአቋም ሰነድ ይፋ ሆኗል። የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ከአርባ ገጽ በላይ የሚሆን በመረጃ የተደገፈ ሰነድ ይፋ አድርጓል። የሰብአዊ መብቶች አለመከበር ለኢትዮጵያና ለአካባቢው ሰላም፤ እርጋታና አብሮ መኖር አደገኛ፤ ለአገሪቱ ዘላቂና ፍትሃዊ እድገት እንቅስቃሴ ማነቆ መሆኑን ጠቅሶ የኢትዮጵያ መንግሥት የኢትዮጵያዊያንን ነጻነት፤ ክብር፤ ህይወት፤ ሰብአዊ መብትና ደህንነት እንዲያከር ጠይቋል። በተመሳሳይ፤ አንድ የአሜሪካ ምክር ቤት ክፍል በኦሮሞያ የተካሄደውን ግድያና ሌላ ተመልክቶ የባለሞያዎች ዘገባ አድርጓል። የተገኙት ባለሞያዎች የኦክላንድ ኢንስቲቱት መስራችና ዲሬክተር፤ የአልጀዚራና የአምነስቲ ኢንተርናሽናል ጋዜጠኞች ነበሩ። በዚህ ውይይት ብዙ መቶ የሚሆኑ የኦሮሞያ ብሄር ተወካዮችና ሌሎች ኢትዮጵያዊያን በተመልካችነት ተገኝተዋል። ውይይቱ ወደ ምክር ቤቱ መደበኛ ዘገባና አቋም ያመራል የሚሉ ተመልካቾች አሉ። ይህ ሊሆን ወይንም ላይሆን ይችላል። የአሜሪካኖቹ ትኩረት አዲስ ፕሬዝደንት ከመምረጡ ላይ ስለሚሆን በምክር ቤት ደረጃ ሌላ አቋም ይወሰዳል የሚል ግምት የለኝም።

የአስራ አንዱ ሴናተሮች አቋም በዚህ ሁኔታ ነው ይፋ የሆነው። ከጥቂት ወራቶች በፊት የአውሮፓ ፓርላማ በኦሮሞያና በሌሎች ቦታዎች የተከሰተውን ሰላማዊ ሕዝባዊ አመፅ፤ ግድያና አፈና በሚመለከት ጠንካራ የሆነ አቋም ወስዷል። የአውሮፓው ምክር ቤትና በአሜሪካ የታወቁ ሴናተሮች ይፋ ያደረጉት አቋም ተመሳሳይነት አለው። ከእነዚህ መካከል፤

አንድ፤ ሁለቱም የኢትዮጵያ መንግሥት የደህንነትና የልዩ ፌደራል ፖሊስ ኃይሎች ያደረጉትን "ግድያ፤ እስራት፤ ማሳደድ" ያወግዛሉ፤ ይህ ሁኔታ እንዲያቆም ያሳስባሉ፤

ሁለት፤ "የታሰሩ ጋዜጠኞች፤ ዲሞክራቶች፤ የሰብአዊ መብት ጠበቃዎች፤ የፖለቲካ ተቃዋሚዎች" በአስቸኳይ እንዲፈቱ ይጠይቃሉ፤

ሶስት፤ "ዝግ የሆነው የፖለቲካውና የማህበረሰብአዊው ምህዳር እንዲለቀቅ፤ የዜጎች የመናገር፤ የመሰብሰብ፤ የመንቀሳቀስ፤ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግና" ተመሳሳይ መብቶች እንዲከፈት ይጠይቃል፤

አራት፤ "የኢትዮጵያ መንግሥት የራሱን ሕገመንግሥት እንዲያከብር" ያሳስባል።

የሴናተሮቹን ውሳኔ (Resolution) ጠንካራ የሚያደርጉ ሁለት አስኳል ጉዳዮች አሉ። አንዱ፤ "የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሃላፊ አሜሪካ ለኢትዮጵያ መንግሥት ለደህንነት፤ ለመረጃ፤ ለፀረ-ሽብርተኛነት መከላከያና ተመሳሳይ የምትሰጠው የመሳሪያ፤ የመረጃና የገንዘብ ድጋፍ" ለተፈለገው ስራ ብቻ እንዲውል፤ ቅርበትና አስተማማኝ ጥናትና ክትትል እንዲደረግበት፤ የሚሰጠው ድጋፍ ለኢትዮጵያዊያን ሰላማዊ ተቃዋሚዎች የማጥቃት ዘመቻ እንዳይውል፤ መስሪያ ቤቱ ይኸን በሚመለከት ለአሜሪካ ምክር ቤት (ሴናት) ሪፖርት እንዲያቀርብ የሚለው ነው።

ሁለተኛው፤ የአሜሪካ የዓለም አቀፍ የእርዳታ መስሪያ ቤት "ለኢትዮጵያ የሚሰጠው እርዳታ "ከሰብአዊ መብቶች መከበር ጋር እንዲያያዝ፤ አሜሪካ እርዳታ በምትሰጥበት አካባቢ የሚኖሩ ነዋሪዎች ከመሬታቸውና ከኑሯቸው እንዳይፈናቀሉ" እንዲያደርግ፤ የአሜርካ እርዳታ የመንግሥት አፈና መሳሪያ እንዳይሆን፤ ድርጅቱ እንደዋና ስራው አድርጎ መያዝ ያለበት "የዲሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ስራዎችና ተቋሞችን ማጠናከር" መሆኑን ተቀብሎ ጉዳዩን የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ኃላፊ እንዲከታተልና ለሴናቱ ሪፖርት እንዲያቀርብ የሚል ይገኝበታል። ይህ ከስራ ላይ ከዋለ ይጠቅማል።

ለማንኛውም የአውሮፓና የአሜሪካ ምክር ቤቶች በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶች መከበር አስፈላጊነት ጉዳይ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ሁሉም ኢትዮጵያዊያን የሚፈልጉት፤ የሚደግፉት፤ የሚያራምዱትና የሚንቀሳቀሱበት ነው። በቅርቡ ለአሜሪካ ፕሬዝደንትነት ተወዳድሮ የነበረው፤ ወደፊት ፕሬዝደንት ለመሆን ተስፋ አለው የሚባለው ወጣቱ ሴናተር ማርኮ ሩቢዮ ፕሬዝደንት ኦባማ በኢትዮጵያ "ታሪካዊ ጉብኝት" ሲያደርጉ ጠንካራ ደብዳቤ እንደጻፈ አስታውሳለሁ። ይህ በ July 22, 2015 የተጻፈ ደብዳቤ እንዲህ ይላል። "Although the United States and Ethiopia share an interest in fighting terrorism and securing stability through the region, it is essential that the U.S. does not turn a blind eye to Ethiopia's human rights abuses. By shutting down avenues to express dissent through the political process, civil society, or media, Ethiopia's government may fuel further instability in the country…..I ask that during your meeting with Ethiopian officials, as well as in any public remarks, that you strongly

